# የሻማ ማብራት ስነ-ሥርአት በፐርት ኦስትራልያ ተካሄደ




ብርቱካን ሚደቅሳንና ሌሎች በሺዎች የሚቆጠሩ በግፍ በወያኔ መንግስት እስርቤት የሚገኙ እስረኞችን በማሰብና ለእነሱ የሚገባውን አክብሮትና ጽኑ ድጋፍ ለመግለጽ ማክሰኞ ሜይ 5 ቀን 2009 ምሽት ላይ በምዕራብ አውስትራሊያ በፐርዝ ከተማ የሻማ ማብራት ስነ-ሥርአት ተካሄደ።

በአምነስቲ ኢንተርናሽናል የምዕራብ አውስትራሊያ ክፍለ ሀገር ጽ/ቤት በተካሄደው በዚሁ ስነ-ሥርአት ላይ አምባገነኑ የወያኔ መንግስት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እየፈጸመ ያለውን የጭካኔ ጥቃት በዝምታ ላለመቀበል የወሰኑ ኢትዮጵያውያንና የክፍለ ሀገሩ የአምነስቲ ባለስልጣኖችና አባሎች ተካፍለዋል።

ተሳታፍዎቹ የብርቱካን ፎቶግራፍ የታተመበትንና በእንግሊዝኛ “ፍሪ ብርቱካን ሚደቅሳ ኤንድ አዘር ፖሊቲካል ፕሪዝነርስ” የሚል መፈክር የሚያስነብብ ቲ-ሸርት በመልበስና የኢትዮጵያን ባንዲራ ከፍ አድርጎ በመያዝ ሻማዎቻቸውን ካቀጣጠሉ በኋላ ለእስረኞቹ የሚሰጡትን ድጋፍ ይበልጥ አጠንክሮ ለመቀጠል ቃል ገብተዋል።

በዚሁ ጊዜ በጨካኙ አገዛዝ መሠረታዊ ሰብአዊ መብቶቿን ተገፋና በጠባብ ክፍል ታፍና የምትሰቃየው ብርቱካን፤ዳኛ ከነበረችበት አንስቶ በኢትዮጵያ አምባገነንነትና ጎጠኝነት ተወግደው ሁሉም ዜጋ ተጠቃሚ የሚሆንበት ፍትሐዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርአት እንዲመሠረት ያደረገችው ጥረትና አስተውጽኦ በተለያዩ ተናጋሪዎች በስፋት ተወስቷል።

ብርቱካን ዛሬ የሕዝቧን መብት ለማስከበር በጽናት በመቆሟ ለብዙዎች የትግል መነቃቂያ አርአያና የተስፋ ምልክት መሆኗ ከመጠቀሱም ባሻገር፤ በዓለም አቀፍ ደረጃም የፀረ-አምባገነንንት ተጋድሎና የነጻነት ወዳድነት ተምሳሌት እየሆነች መምጣቷ ተሰምሮበታል።

በምዕርብ አውስትራሊያ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ምክትል ፕሬዚደንት ሚስተር ግሬግ ስቲት በስነ-ሥርአቱ ላይ እንደገለጹት፡፤ ብርቱካን የምትገኝበትን አስከፊ ሁኔታ ከተረዱት ወራት የተቆጠሩ መሆኑን አመልክተው፤ሁኔታው አሳሳቢነቱ የቀጠለ በመሆኑ ከአምነስቲ ጋር በሚተባበሩ ማህበረሰቦችና አካላት ዘንድ ግንዛቤ እንዲያገኝና የጋራ ጥረት እንዲካሄድበት የተለያዩ መልእቶችን እያስተላለፉ መሆኑን አስታውቀዋል።

የክፍለ ሀገሩ አምነስቲ የሴቶች ጥቃት መከላከያ ዘርፍ የዘመቻ አስተባባሪ የሆኑት ሚስስ ኤሪካ ጀኮብሰን በበኩላቸው የብርቱካን መታሰር ባለፈው ማርች 8 ዓለምአቀፍ የሴቶች ቀን ሲከበር በብዙ የበዓሉ ተካፋይ ሴቶች መታወቁን አውስተው፤ እሷን ለማስፈታት በሚደረገው ትግል አባሎቻቸው የሚሳተፉ መሆኑን አረጋግጠዋል።

በመጨረሻም ተሳታፍዎቹ ወያኔ በዚህ ወቅት የተለያዩ ሰበቦችን እየፈጠረ ጠንካራ የሕዝብ ወገን ናቸው ብሎ ያሰባቸውን ሁሉ እየለቀመ በማሰርና በማጥፋት ላይ መሆኑ እጅግ ያሳሰባቸው መሆኑን አመልክተው፤ ብርቱካንና ሌሎች እስረኞች ሁሉ በአስቸኳይ እንዲፈቱና በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት እንዲከበር አጠንክረው እንደሚታገሉ በመግለጽ ስን-ሥርአቱን አጠናቀዋል።

አዘጋጅ ኮሚቴ